# Guidance For Fasting Muslim

## የፆመኛ ሙስሊም መመሪያ




***Presented by: Youth-Mission Online Amharic Islamic Books Publishing.***

## Guidance For Fasting Muslim

## የፆመኛ ሙስሊም መመሪያ

**All right reserved**

© የወጣቱ ተልዕኮ

የወጣቱ ተልዕኮ አንላይን እትም 2008

ሰሜን ወሎ ወልዲያ

ahmedyesuf29@gmail.com

+251927790323

http://youth-mission.mobie.in

የሰው ልጅ ያለ መመሪያና ደንብ ልጓም እንደሌለው ፈረስ በመሆኑ በየትኛውም የህይወት ዘርፍ የሰው ልጅ መመሪያ ያስፈልገዋል።

ሆኖም ፆመኛ ሙስሊም እንደሌሎቹ የእምነቱ ስርአት ሊከተላቸውና ሊተገብራቸው የሚገቡ መመሪያና ደንቦች እንደሚከተለው ተብራርተዋል።

# የፆመኛ ሙስሊም መመሪያ

## በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

## በሸኽ ሙሐመድ ቢን ሷልህ አል-ኡሰይሚን

## ትርጉም በአህመድ የሱፍ

ምስጋና ለአለማት ጌታ ለአሏህ ይገባው። የአሏህ ሰላምና እዝነት የነብያቶች መደምደሚያ በሆኑት በነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ፣ በቤተሰቦቻቸውና በሶሃቦቻቸው ላይ ይሁን።

ማንኛውም ሙስሊም ሊያውቃቸው የሚገቡ ጠቃሚ የፆም ህግጋቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## ፆም ምንድነው?

ሲያም(ፆም)_ ከንጋት ጀምሮ ፀሐይ እስከምትጠልቅበት ጊዜ ድረስ ከምግብ ፣ ከመጠጥ እና ከግብረስጋ ግኑኙነት እንዲሁም ከሃራም ነገሮች ሁሉ በመቆጠብ አሏህን መገዛት ነው።

## የፆም ጥቅም

የረመዷን ፆም አንዱ የኢስላም ምሶሶ ነው። ይህን በተመለከተ የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) ኢስላም የተመሰረተው(የተገነባው) በአምስት ምሶሶዎች ላይ ነው ብለዋል። እነሱም፡-

1. ከአሏህ ውጭ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) የአሏህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር።
2. ሶላት መስገድ
3. ዘካ መክፈል
4. ሐጅ ማድረግና
5. በረመዷን ወር መፆም ናቸው።

## የፆም ህግጋቶች

**1** ፆም ጎልማሳ በሆነ ፣ ጤናማ አዕምሮ ባለውና መፆም በሚችል ማንኛውም ሙስሊም ወንድም ሆነ ሴት ላይ ግዴታ ነው።

**2** አማኝ ያልሆነ ሰው አይፆምም፤ ቢፆምም ተቀባይነት የለውም። ምናልባት አሏህ ቀጥተኛውን መንገድ መርቶት ኢስላምን ቢቀበል ያለፉትን የፆም ቀናት ማካካስ አይጠበቅበትም።

**3** ፆም ለህፃናት ግዴታ አይደለም። ነገርግን ይለምዱት ዘንድ እንዲፆሙ መበረታታት ይኖርባቸዋል።

**4** አዕምሮው የተዛባ ሰው መፆምም ሆነ ሰዎችን በመመገብ ማካካስ አይገደድም።

**5** ለዘለቄታው መፆም የማይችሉ ሰዎች ለምሳሌ በጣም ያረጁና ስር በሰደደ ህመም እየተሰቃዩ ምንም የማገገም ተስፋ የሌላቸው ሰዎች በመፆም ፈንታ ድሆችን መመገብ ይጠበቅባቸዋል።

**6** ታሞ የማገገም ተስፋ የሌለው ሰው ፆሙ አስቸጋሪ ከሆነበት ፆሙን ሊያፈርስ ይችላል። ሆኖም ግን ካገገመ

ብኋላ ያለፈውን ቀን ማካካስ ይኖርበታል።

**7** ነፍሰጡር ሴቶችና ጡት የሚያጠቡ እናቶች በረመዷን ወቅት መፆም አስቸጋሪ ከሆነባቸው ወይም ልጁ ይጎዳብኛል ብለው ከፈሩ ፆማቸውን መፍታት ይፈቀድላቸዋል። ብኋላ ላይ ግን ያለፋቸውን ቀናት ማካካስ ይኖርባቸዋል።

**8** የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ላይ የሆኑ ሴቶች በዚህ ወቅት መፆም አይፈቀድላቸውም። ነገርግን ብኋላ ላይ ያለፋቸውን ቀናት ማካካስ ይገደዳሉ።

**9** ምንገደኛ ሰው መፆም ወይም ደግሞ አለመፆም የሚችል ሲሆን ካልፆመ ብኋላ ላይ ያለፉትን ቀናት ማካካስ ይኖርበታል።

## ፆምን የሚያበላሹ ነገሮች

ፆመኛ ሁነን ሳናስበው ዘንግተን(ረስተን) ብንበላ ወይም ብንጠጣ ወይም ደግሞ ተገደን እንድንበላና እንድንጠጣ ብንደረግ ፆማችን አይበላሽም። ሃያሉ አሏህ በቁዱስ ቁርአን እንዲህ ይላል፦

=<(፤አል-ቁርአን 2:286፤)>=

፤286፤ ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንስት አትያዘን(አትቅጣን) (በሉ)።

=<(፤አል-ቁርአን 16:106፤)>=

፤106፤ ልቡ በኢማን ረግታ ይህን እንዲያደርግ ከተገደደ ሰው በቀር

=<(፤አል-ቁርአን 33:5፤)>=

፤5፤ ልባችሁ ሆንብሎ ባሰበው እንጅ ሳታውቁ በሰራችሁት ስህተት ሃጢያት የለባችሁም።

ስለዚህ ሳናውቅ ረስተን ብንበላ ወይም ብንጠጣ ፆማችን አይበላሽም። እንዲሁም ፀሐይዋ በመጥለቋ ምሽቱ ጀምሯል ብለን በማሰብ ብንበላና ብንጠጣ ወይም ደግሞ ንጋቱ ገና እንዳልጀመረ አስበን ብንበላ ብንጠጣ ፆማችን አይበላሽም። በተመሳሳይ መልኩ እየፆምን እንዳለ የዘር ፈሳሻችን ሳናስበው ቢፈስ ፆማችን አይበላሽም።

## *ፆም የሚያበላሹ ነገሮች ምንድን ናቸው?*

ፆም በሚከተሉት ስምንት ነገሮች ይበላሻል።

1 ግብረ ስጋግኑኝነት ማድረግ: ፆም ግዴታ የሆነብን ሰዎች በረመዷን ቀን ላይ ወሲብ ከፈፀምን ይህን ቀን ማካካስና መቶበት ይኖርብናል። ያለፈንን ቀን ለማካካስ አንድ ባርያ ነፃ ማውጣት ይጠበቅብናል። ይህን ማድረግ ካልቻልን ሁለት ወር በተከታታይ መፆም ይኖርብናል። ይህንንም ማድረግ ካልቻልን ስልሳ ድሆችን መመገብ ይኖርብናል።

2 ሆንብሎ የዘር ፈሳሽን ማፍሰስ: ለምሳሌ ከራስ ብልት ጋር በእጅ በመጫወት ፣ በመሳምና በማቀፍ

3 ሆንብሎ መብላት መጠጣት

4 የምግብ መርፌ መወጋት ፆም ያበላሻል። ምክኒያቱም

ከመብላትና ከመጠጣት ጋር ተመሳሳይ ነውና።

5 ደም መለገስ (መስጠት)፡ ፆመኛ ሰው በሰውነቱ ውስጥ ብዙ ደም ፈሶት እንዲያገግም ደም ቢለገሰው ፆሙ ይበላሻል።

6 የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም

7 የዋግምት ደም መፍሰስ፡ ደም በራሱ ጊዜ ከአካል ከፈሰሰ ፆም አያበላሽም። ለምሳሌ የነስር ደም ወይም ደግሞ ጥርስ ከተነቀለ ብኋላ የሚፈስ ደም

8 ጣታችነን ወደ ጉሮሯችን በማስገባት ሆንብለን እንዲያስታወከን ብናደርግ ፆማችን ይበላሻል። ሳናስበው በድንገት ቢያስታውከን ግን ፆማችን አይበላሽም።

## ጠቃሚ መረጃዎች

1 የፆም ንያን ጀናባ በሆንበት ጊዜ ቢሆንኳ መነየት የምንችል ሲሆን ከንጋት ብኋላ መታጠብ እንችላለን።

2 የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ምሽት ላይ ያቆመላት ሴት ቀጣዩን ቀን ለመፆም መነየት ይኖርባታል። ጉሱል(ሙሉ ትጥበት) እስከ ንጋት ድረስ ማዘግየት

ትችላለች። ነገርግን ሙሉ ትጥበቷን ከፈጅር ሶላት በፊት መፈፀም ይኖርባታል።

3 ፆመኛ ሰው ጥርሱን መንቀል ፣ ቁስሉን ወይም ጉዳት የደረሰበትን የአካል ክፍል ማከም ፣ የአይን ጠብታ መጠቀም ይችላል። ሆኖም የአይን ጠብታው ጣዕም በጉሮሮው ቢወርድ ፆሙ አይበላሽም።

4 ፆመኛ ሰው ሲዋክ ወይም የጥርስ ብሩሽ በመጠቀም ጥርሱን ማፅዳት ይችላል። ቀኑን ሙሉ ወይም ከሶላት በፊት ጥርስን በሲዋክ መፋቁ ሱና ነው።

5 ፆመኛ ሰው በሞቃት የአየር ንብረት ወይም በውሃ ጥም ቢቃጠል ይህን የሚያቀልለትን ነገር ማድረግ የሚችል ሲሆን ሰውነቱን ለማቀዝቀዝ ውሃ ወይም የአየር ማቀዝቀዣ መሳሪያ መጠቀም ይፈቀድለታል።

6 በጭንቀት ወይም በሌላ ችግር ምክኒያት የመተንፈስ ችግር ያጋጠመው ፆመኛ የአተነፋፈስ ስርአቱን ለማስተካከል አፉ ውስጥ የሆነ ነገር መርጨት ወይም መሳብ ይችላል።

7 አፍን መጉመጥመጥና አፍንጫን ወይም የደረቁ ከናፍሮችን በውሃ ማርጠብ ይፈቀዳል። ነገርግን እየፆመ በተጋነና መልኩ ብዙ ውሃ በጥልቀት ወደ አፍ ወይም

ወደ አፍንጫ ማድረስ የተጠላ ነው።

8 ፀሐይ እንደጠለቀች ያለምንም ማዘግየት ወዲያውኑ ማፍጠር (ፆምን መፍታት) ሱና ነው።

9 በፆም ወቅት ብዙ መልካም ስራዎችን አብዝቶ መስራትና የተከለከሉ ነገሮችን ሁሉ መራቅ ሱና ነው።

10 ፆመኛ ሰው ዋጅብ (ግዴታ) የሆኑ ስራዎችን ሁሉ መስራት እና ከተከለከሉ ነገሮች ሁሉ መራቅ ይኖርበታል። ለምሳሌ የቀኑን አምት ስግደቶች በጀመአ መስገድ ይኖርበታል። ከተከለከሉ ነገሮች ደግሞ ለምሳሌ ሐሜት ፣ ውሸት መናገር ፣ ማታለል፣ አራጣ መብላት ወ.ዘ.ተ መከልከል ይኖርበታል። ይህን በተመልከተ የአሏህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) "ውሸት መናገርና መጥፎ ስራዎችን መስራት ያልተወ ሰው አሏህ ምግብና መጠጥ መተውን አይፈልግም" ብለዋል።

## ዘካቱል ፊጥር ምንድነው?

ዘካቱል ፊጥር ማንኛውም መክፈል የሚችል ሙስሊም በእራሱና በእያንድንዱ የቤተሰቡ አባል ስም በተናጠል ከረመዷን መጨረሻ ላይ ከኢድ ሶላት በፊት ሊከፍለው

የሚገባ ግዴታ የሆነ የድሆች መዋጮ ምፅዋት ነው።

## የዘካቱል ፊጥር አከፋፈል ሁኔታ

የዘካቱል ፊጥር ክፍያ መሰረታዊ ፍላጎቱን ከሚያሟላበት በላይ የሆነ ሶስት ኪሎግራም ተምር ወይም ገብስ ወይም ደግሞ ተመሳሳይ የምግብ እህሎች ባሉት ማንኛውም ሙስሊም ላይ ግዴታ ሲሆን መክፈል የሚችል ሰው በእራሱና ቤተሰብ የመያስተዳድር ከሆነ በእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ስም በተናጠል መክፈል ይኖርበታል። ነገርግን ከቤተሰቡ አባል ውስጥ በራሱ መክፈል የሚችል ሰው ካለ በእራሱ ስም መክፈሉ በላጭ ነው። ከእናቱ ማህፀን ውስጥ ባለ ልጅ ስም ሊከፍል ይችላል ነገርግን ግዴታ አይደለም። ኡስማን ኢብን አፋን(ረ.ዐ) ማህፀን ውስጥ ባለው ልጁ ስም ዘካቱል ፊጥር ይከፍል ነበር።

ስለዚህ የዘካቱል ፊጥር ክፍያ መጠን ሶስት ኪሎ የሆነ ገብስ ፣ በቆሎ ፣ ሩዝ ፣ ወይም ደግሞ ሌላ የምግብ አይነት ሊሆን ይችላል። ነገርግን ምግብ ያልሆነ ልክ እንደ ልብስ ወይም የቤት እቃ ያሉ ነገሮችን መክፈል አይቻልም።

## ለማነው የሚሰጠው?

ዘካው ሊከፋፈል የሚገባው ዘካው በተከፈለበት ሐገር ውስጥ ለሚኖሩ ችግረኞችና ድሆች ነው። ሆኖም ግን ከፋዩ ካለበት ቦታ ችግረኞችን ወይም ድሆችን ካላወቀ ሌላ ቦታ ላሉ ችግረኞች ወይም ድሆች መከፈል ይችላል።

## የሚከፈልበት ጊዜ

ዘካቱል ፊጥር የሚከፈልበት ጊዜ ከኢድ ቀን ቀደም ብሎ ሲሆን የኢድ ቀን ሶላቱ ከመሰገዱ በፊት ጧት ላይ መከፈሉ ተመራጭ ነው። ይሁን እንጅ ከኢድ በፊት አንድ ወይም ሁለት ቀን ቀደም ብሎ መከፈል ይፈቀዳል።

የዘካቱል ፊጥር ክፍያ ያለምንም ተጨባጭ ምክኒያት ከኢድ ሶላት ብኋላ ለመክፈል ማዘግየት አይፈቀድም። የኢድን ዜና ዘግይቶ ካወቀ ወይም ዘካቱል ፊጥር ማንም የማይቀበልበት ቦታ ከሆነ ያለው ብኋላ ላይ ሊከፍለው ይችላል። ያለምንም ተጨባጭ ምክኒያት ክፍያውን ያዘገየ ግን ክፍያው እንደ ዘካቱል ፊጥር ሳይሆን የሚቆጠርለት

እንደ ሶደቃ ነው የሚታሰበው። ዘካውን መክፈል ይኖርበታል ነገርግን የዘካቱል ፊጥርን ልዩ ምንዳ አያገኝም።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከሶላት (ከኢድ ሶላት) በፊት ዘካ የከፈለ ሰው ተቀባይነት እንዳገኘ ዘካ ይቆጠርለታል። ከሶላት (ከኢድ ሶላት) ብኋላ የከፈለ ሰው እንደ ሶደቃ ይቆጠራለታል ብለዋል። ይህ ሐዲስ በአቡዳውድ ፣ በነሳኢና በኢብን ማጃ ተዘግቧል።

## ዘካቱል ፊጥርን የተመለከቱ ውሳኔዎች(ደንቦች)

የአንድን ሰው ዘካቱል ፊጥር ክፍያ ለተወሰኑ ድሆች ማከፋፈል ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን የዘካቱል ፊጥር ክፍያ ለአንድ ሰው መስጠት ይፈቀዳል። እዲሁም የዘካቱል ፊጥር ክፍያን አንድ እቃ ላይ ሰብስቦ ሳይለኩ ለድሆች ማከፋፈል ይችላሉ።

መጥፎ ነገሮችን በዘካቱል ፊጥር መልክ መክፈል አይፈቀድም። አሏህ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 2:267})>=**

**{267} እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ካገኛችሁት መልካም ነገር እና ከምድር ካወጣንላችሁ ፍራፍሬዎች ስጡ። መጥፎውን ነገር አይናችሁን ጨፍናችሁ እንጅ የማትቀበሉት ሲሆን ለመስጠት አታስቡ። አሏህ የተብቃቃ ምስጉን መሆኑን እወቁ።**

ማንኛውም አይነት አስተያየት ፣ ትችትና ነቀፌታ ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወሉልኝ ይችላሉ። ተጨማሪ የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.mobie.in ይጎብኙ። ጀዛኩሙለህ ኸይረን ከሲረን!